## የጥርስ አገልግሎቶች

Smile Squad ነጻ የጥርስ አገልግሎቶችን ብቃት ባላቸው ባለሞያዎችን በቪክቶሪያ መንግስት ትምህርት ቤትዎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች ይሰጣል።

## የጥርስ ሕክምና ምርመራዎች (ምርመራ)

የጥርስ ህክምና የጥርስ፣ የድድ፣ የመንጋጋ እና የአፍ ምርመራን ያካትታል።

**ጥቅማጥቅሞች፡-**አብዛኛዎቹ የአፍ ውስጥ በሽታዎች / የጥርስ ችግሮች በመጀመሪያዎቹ ደረጃዎች ላይ ህመም አያስከትሉም። ችግሮችን ቀደም ብሎ ለማግኘት መደበኛ ምርመራዎች በጣም ጥሩው መንገድ ናቸው። አንዴ ምን እየተፈጠረ እንዳለ ካወቅን በኋላ፣ ለክትትል ህክምና ማቀድ እንችላለን።

ፈቃድ ከሰጡ፣ ተማሪን የሚጠቅሙ ከሆነ የሚከተሉት አገልግሎቶች ሊሰጡ ይችላሉ፡-

## የጥርስ የኤክስሬይ

የኤክስሬይ ማሽን በሰውነት ውስጥ ምን እየተከናወነ እንዳለ የሚያሳይ ምስል ለመፍጠር ጨረር ይጠቀማል።

በአፍ ውስጥ የተቀመጠ ትንሽ ፊልም በመጠቀም የጥርስ ራጅ እንይዛለን።

**ጥቅማጥቅሞች፡-**ኤክስሬይ በአይን ሊታዩ ስለማይችሉ ጥርሶች መረጃ ይሰጠናል። ኤክስሬይ መበስበስ፣ ኢንፌክሽን እና ሌሎች ችግሮችን ማግኘት ይችላል።

**ስጋትዎች፡-**ኤክስሬይ ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው። በተለምዶ የምንወስዳቸው የራጅ ጨረሮች ከአውሮፕላን በረራ ያነሰ ጨረር አላቸው።

## የፍሎራይድ ቫርኒሽ ትግበራ

ፍሎራይድ ቫርኒሽ ቢያንስ በየስድስት ወሩ ቢተገበር በተሻለ ሁኔታ የሚሰራ የመከላከያ ህክምና ነው።

የፍሎራይድ ቫርኒሽን በጥርሶች ላይ መቀባት በጣም ቀላል እና ብዙ ጊዜ ጥቂት ደቂቃዎችን የሚወስድ ነው። ቫርኒሽ በጥርስዎ ላይ እስኪቦርሿቸው ድረስ ተጣብቀው ይቆያሉ።

**ጥቅማ ጥቅሞች፡-** ፍሎራይድ ጠንካራ ጥርስ ለመገንባት እና የጥርስ መበስበስን ለመከላከል የሚረዳ የተለመደ ማዕድን ነው። ፍሎራይድ ቫርኒሽ መበስበስን ከመጀመሩ በፊት ሊያቆም እና የመበስበስ ሁኔታን ሊያዘገይ ይችላል።

**ስጋትዎች፡-**አልፎ አልፎ ቢሆንም፣ አንዳንድ ሰዎች በፍሎራይድ ቫርኒሽ ውስጥ ላለው ንጥረ ነገር አለርጂ ናቸው። ለኮሎፎኒ/ሮሲን፣ ካሴይን(የወተት ፕሮቲን) ወይም ከባድ አስም አለርጂ ያለባቸው ተማሪዎች የፍሎራይድ ቫርኒሽ ሊኖራቸው አይችልም።

## ስንጥቅ ማሸጊያዎች

ማሸጊያዎች በጥርሶች ላይ ባሉ ቡርቡሮች (ፊሸር) ላይ የተቀቡ ቅቦች ናቸው። ብዙውን ጊዜ የሚቀመጡት በመንጋጋ ጥርስ ላይ ነው።

**ጥቅማጥቅሞች፡-** ማሸጊያዎች የጥርስን ቡርቡሮች በመሸፈን ምግብ እና ጀርሞችን ገብቶ ከመቅረት ያቆማሉ። ይህም መበስበስን ከመጀመሩ በፊት እና በቡርቡሮች ውስጥ ቀመሰራጨቱ በፊት ያስቆማል።

አብዛኛዎቹ የማሸጊያ ቁሶች ፍሎራይድ የያዙ ናቸው። ማሸጊያዎች በጊዜ ሂደት ሊጠፉ ይችላሉ እና መሙላት ወይም መተካት ሊኖርባቸው ይችላል።

## የጥርስ ጽዳት

ጥርስን በመቦረሽ ካልኩለስ (ደረቅ ንጣፍ) ወይም ጠንካራ እድፍ ማስወገድ በማይቻልበት ጊዜ ጥርሶች ተጨማሪ ጽዳት ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

**ጥቅማጥቅሞች፡-**ድዶችን የሚያስቆጣ ካልኩለስን በማስወገድ ለድድ በሽታ ተጋላጭነትን መቀነስ እንችላለን።

## የክትትል ሕክምና

ተጨማሪ ሕክምና ካስፈለገ፣ Smile Squad ይህንን ከእርስዎ ጋር በመወያየት ፍቃድዎን ይጠይቃል።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### ወላጆች፣ ህጋዊ አሳዳጊዎች ወይም ተንከባካቢዎች በተማሪው ቀጠሮ ላይ መገኘት አለባቸው?

ወላጆች፣ ህጋዊ አሳዳጊዎች ወይም ተንከባካቢዎች ከፈለጉ መሳተፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህ መስፈርት አይደለም።

ለመሳተፍ ከፈለጉ እባክዎ እኛን ለማሳወቅ Smile Squad ያነጋግሩን።

ተጨማሪ ሕክምና ካስፈለገ፣ ወላጅ፣ ህጋዊ አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ ወደ ቀጠሮው እንዲመጡ ልንጠይቅ እንችላለን።

### አንድ ተማሪ በቅርብ ጊዜ የጥርስ ህክምና አድርጎ የነበረ ቢሆንስ?

አንድ ተማሪ በቅርብ ጊዜ የጥርስ ህክምና ጉብኝት ያደረገ ቢሆንም በSmile Squad እንደገና ሊታይ ይችላል። ኤክስሬይ እና ሌሎች የመከላከያ አገልግሎቶች ላያስፈልጓቸው ይችላል።

### በSmile Squad ጉብኝት ወቅት ተማሪው በትምህርት ቤቱ ባይገኝስ?

አንድ ተማሪ በትምህርት ቤቱ ካልተገኘ፣ ሌላ ቀን እናገኛቸዋለን ወይም በአካባቢያቸው የማህበረሰብ የጥርስ ህክምና ኤጀንሲ ሊያገኙን ይችላሉ። እነዚህ አገልግሎቶች አሁንም ነጻ ናቸው።

በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የማህበረሰብ የጥርስ ክሊኒክ በዚህ ያግኙ፡- [www.dhsv.org.au/our-services/find-dental-clinics/clinic-search](www.dhsv.org.au/our-services/find-dental-clinics/clinic-search)

### ፍቃድ የሚሰጠው ማን ነው?

ወላጆች፣ ህጋዊ አሳዳጊዎች ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሱ በሳል ልጆች እነዚህን ቅጾች ሞልተው ፈቃድ ሊሰጡ ይችላሉ።

ለአካለ መጠን ያልደረሰ በሳል ሰው ለመባል፣ የሕክምና ባለሙያው ተማሪው ስለ ጉዳቶች፣ ጥቅሞች እና በሁኔታቸው ምክንያት ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ችግሮች እና ስለታሰበው ህክምና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነት ለመስጠት በቂ ግንዛቤ እንዳለው ማመን አለበት።

አንድ ተማሪ አንዳንድ የጥርስ ህክምና ውሳኔዎችን መወሰን ይችላል ተብሎ ሊታሰብ ይችላል ነገር ግን ሌሎች ነገሮችን አይችልም። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜ ያለው ተማሪ በህክምና ባለሙያው እንደ አዋቂ የማይቆጠር ከሆነ፣ ከወላጅ ወይም ከህጋዊ አሳዳጊ ፈቃድ የሚጠየቅ ይሆናል።

# የልጅ የጥርስ ህክምና ጥቅሞች መርሃ ግብር(CDBS)

አንዳንድ ተማሪዎች በMedicare በኩል፣ ለአውስትራሊያ መንግስት የህጻናት የጥርስ ጥቅማ ጥቅሞች መርሃ ግብር (CDBS) ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

በ(CDBS) የስምምነት ፎርሙን ከፈረሙ የአውስትራሊያ መንግስት ለዚህ የጥርስ ህክምና እርስዎን ወክለን የይገባኛል ጥያቄ እንድናቀርብልዎት ይፈቅድልናል።

**የልጅ የጥርስ ህክምና ጥቅሞች መርሃ ግብር(CDBS) ምንድን ነው?**
CDBS ከ0–17 አመት ለሆኑ ህጻናት መሰረታዊ የጥርስ ህክምና በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ የMedicare ፕሮግራም ነው።

ተማሪዎች (CDBS)ሳቸውንለሚከተሉት መጠቀም ይችላሉ፦-

- ለSmile Squad አገልግሎቶች
- በቪክቶሪያ የህዝብ የጥርስ ህክምና ክሊኒክ
- በግል የጥርስ ሕክምና ክሊኒክ

Smile Squad ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች (CDBS) ይጠቀማል።

የ(CDBS) የስምምነት ቅጹን ባይፈርሙ እንኳ፣ እያንዳንዱ ተማሪ አሁንም ከSmile Squad ነፃ የጥርስ ሕክምና ያገኛል። **ለእርስዎ ምንም ወጪ አይኖርም።**

Smile Squad በMedicare ስር ወጪዎችን እንዲጠይቅ ለማስቻል የጅምላ ክፍያን የ(CDBS) ስምምነት ቅጽ ላይ እንዲፈርሙ እናበረታታዎታለን። ይህ ለብዙ ቪክቶሪያውያኖች የጥርስ ሕክምና ለመስጠት ይረዳናል።

**ለማጣቀሻ የጅምላ ክፍያ ወጪዎች**
Medicare ይህንን መረጃ እንድንሰጥዎት ይፈልጋል። (CDBS)ን ከተጠቀሙ እነዚህ መጠኖች ከ(CDBS) የጥቅማጥቅም ገደብዎ ላይይወሰዳሉ፦-

| አገልግሎት | (CDBS) በጅምላ የሚከፈል ክፍያ | የሚከፍሉት መጠን |
|---|---|---|
| የጥርስ ሕክምና ምርመራዎች(ምርመራ) | $57.65 | $0.00 |
| የጥርስ ኤክስሬይ (አስፈላጊ ከሆነ) | $33.35 በ ኤክስሬይ | $0.00 |
| የስንጥቅ ማሸጊያዎች (አስፈላጊ ከሆነ) | $50.45 (በቢዛ) በአንድ ጥርስ | $0.00 |
| የጥርስ ጽዳት (አስፈላጊ ከሆነ) | $98.20 (ቢበዛ) እንደ አስፈላጊው የጽዳት ደረጃ ይወሰናል | $0.00 |
| ፍሎራይድ ቫርኒሽ ለሁሉም ጥርሶች (አስፈላጊ ከሆነ) | በአንድ ትግበራ $37.85<br>(በ12 ወራት ውስጥ እስከ ሁለት ትግበራዎች) | $0.00 |

# ግላዊነት

የጥርስ ጤና አገልግሎት ቪክቶሪያ(DHSV) ከማህበረሰብ የጥርስ ህክምና ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር Smile Squadን አያቀረበ ነው። (DHSV) ለSmile Squad ታካሚ ሰነዶች ሃላፊነቱን ይወስዳል። (DHSV) የእርስዎን ግላዊነት ያከብራል እና የእርስዎን መረጃ ለመጠበቅ ቁርጠኛ ነው። መረጃዎን *በጤና መዝገቦችህግ እና በግላዊነት እና በመረጃ ጥበቃ ህግ* መሰረት እናስተናግዳለን።

በተወሰኑ ጊዜያት ለSmile Squad ምርምር እና ግምገማ ዓላማዎች እና አገልግሎቶቻችንን ለማሻሻል ውሂብ እና ግብረመልስ እንሰበስባለን። ለዚህ ማንነታትዎን እንዳይታወቅ እናደርጋለን።

እንደ (DHSV)፣ የትምህርት መምሪያ እና የጤና ጥበቃ መምሪያ ላሉ የመንግስት ኤጀንሲዎች እንዳይታወቅ የተደረገውን መረጃዎን ማጋራት አለብን። ይህንን የምናደርገው በቪክቶሪያ ውስጥ በትምህርት ቤት ስለሚገኙ ተማሪዎች ሁሉ የአፍ ጤንነት በጋራ እንድንማር ነው። ማንኛውንም ማንነት የሚገልጽ መረጃ እናስወግዳለን።

የ(DHSV)ን ሙሉ የግላዊነት መግለጫ ለማንበብ እዚህ ይጎብኙ Www.dhsv.org.au/privacy ወይም ከታች ያለውን የQR ኮድ ስካን ያድርጉ፦-

**መብቶች እና ግዴታዎች**
የጤና እንክብካቤ መብቶችዎ ቅጂ በአውስትራሊያ በጤና እንክብካቤ ላይ የደህንነት እና ጥራት ኮሚሽን ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል።

# በSmile Squad ውስጥ ለመሳተፍ ይህን የስምምነት ቅጽ ይፈርሙ



**የትምህርት ቤቱ ስም፦** ______________________________ **ክፍል (ለምሳሌ 2B):-** ______________________________

**የተማሪው ሙሉ ስም:** ______________________________ **የተማሪው የልደት ቀን:-** ____ / ____ / ____

ከላይ የተጠቀሰው ተማሪ በSmile Squad ትምህርት ቤት የጥርስ ህክምና ፕሮግራም ላይ እንዲሳተፍ ፍቃድ ሰጥቻለሁ።

ተማሪው የሚከተሉትን አገልግሎቶች እንዲያገኝ ፈቃድ ሰጥቻለሁ:-

**የጥርስ ሕክምና ምርመራ** (ምርመራ) ☐ አዎ ☐ አይ

ማስታወሻ:- ሌላ ማንኛውም አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ለጥርስ ሕክምና አዎን ማለት አለበት።

**የጥርስ ኤክስሬይ** (ከተፈለገ) ☐ አዎ ☐ አይ

**የፍሎራይድ ቫርኒሽ** (ካስፈለገ) ☐ አዎ ☐ አይ

**የስንጥቅ ማሸጊያዎች** (ካስፈለገ) ☐ አዎ ☐ አይ

**ጥርስ ማጽዳት**(አስፈላጊ ከሆነ) ☐ አዎ ☐ አይ

> ቀጣዩን ትውልድ የአፍ ጤና ባለሙያዎችን እያሰለጠንን ነው። ተማሪዎች በጥርስ ህክምና/የአፍ ጤና ተማሪ በብቁ የSmile Squad የክሊኒክ ባለሞያ ቁጥጥር ስር ሲሰሩ ሊታዩ ይችላሉ።
>
> ተማሪው በጥርስ ህክምና/የአፍ ጤና ተማሪ እንዲታይ ተስማምተዋል? ☐ አዎ ☐ አይ

እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ Smile Squad ተገቢውን እንክብካቤ ለመስጠት የሚያስፈልጉትን ሁሉንም ተዛማጅ የጤና እና የግል መረጃዎች እንዳቀረብኩ ተስማምቻለሁ።

ስምምነትን ስሰጥ፣ በዚህ ጥቅል ውስጥ ያለውን ይህን የስምምነት ቅጽ እና መረጃ እንዳነበብኩ ተስማምቻለሁ። የሚከተሉትን ለመረዳት በቂ መረጃ አለኝ:-

## የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶች

በSmile Squad የሚሰጡትን የጥርስ ሕክምና ዓይነቶች፣ አብረው የሚመጡትን ጥቅሞች እና አደጋዎች፣ አገልግሎቶቹ የት እንደሚከናወኑ፣ እና ማን እንደሚሰጣቸው አውቃለሁ። የሚሰጡት ሁሉም አገልግሎቶች ነጻ ናቸው።

## ከሕክምና አገልግሎቶች በኋላ የሚሰጥ እንክብካቤ

አንድ ተማሪ የጥርስ ህክምና አገልግሎት ከተቀበለ በኋላ በትምህርት ቤት ከታመመ ወይም በት/ቤት ሊተዳደር የማይችል ተጨማሪ እንክብካቤ የሚያስፈልገው ከሆነ የSmile Squad የክሊኒክ ባለሞያ ወይም የት/ቤት ሰራተኛ ወላጆችን፣ ህጋዊ አሳዳጊዎችን ወይም ተንከባካቢዎችን ሊያነጋግሩ እንደሚችሉ ይገባኛል።

## ግላዊነት

በዚህ ጥቅል ውስጥ ያለውን የግላዊነት መረጃ አንብቤ ተረድቻለሁ እና ፕሮግራሙ የተማሪ ጤና አጠባበቅ መረጃን እንዴት እንደሚያስተዳድር አረጋግጫለሁ።

**የወላጅ/አሳዳጊ/ተማሪ* ፊርማ:-** ____________________________________________

**የወላጅ/አሳዳጊ/ተማሪ* ሙሉ ስም:-** ______________________________ **ቀን:-** ____ /____ / ____

* ዕድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ተማሪዎች እና ለአካለ መጠን ያልደረሱ በሳል ልጆች የጥርስ ህክምና አገልግሎት ለማግኘት ሲሉ ለራሳቸው ፈቃድ መስጠት ይችላሉ። ይህ ስምምነት ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ለ12 ወራት ያገለግላል።

መረጃ ብቻ
ለክሊኒክ የፍቃድ ቅጹን የእንግሊዝኛውን ቅጂ በመሙላት ይመልሱ

**የትምህርት ቤት ስም፦** ______________________ **ክፍል (ለምሳሌ 2B)፦** ______________________

## የተማሪ መግለጫዎች

**የመጀመርያ ስም፦** ______________________ **የቤተሰብ ስም፦** ______________________

**ጾታ፦** ☐ **ወንድ** ☐ **ሴት** ☐ **ሌላ፣** ካለ ያብራሩ ______________________ **የትውልድ ቀን፦** ____ / ____ /____

**የተማሪው ተመራጭ የግል ተውላጠ ስሞች ምንድናቸው?** (ግዴታ አይደለም) ______________________

**አድራሻ፦** ______________________

**ከከተማ ወጣ ያለ ስፍራ፦** ______________________ **ፖስታል ኮድ፦** ______________________

ለራስዎ ፈቃድ የሚሰጡ ተማሪ ከሆኑ፣ እባክዎን የሚከተሉትን ያካቱ፦

**የስልክ ቁጥር፦** ______________________ **ኢሜል፦** ______________________

## የወላጅ/አሳዳጊ መግለጫዎች

**የመጀመርያ ስም፦** ______________________

**የቤተሰብ ስም፦** ______________________

**ከተማሪው ጋር ያለ ግንኙነት፦** ______________________

**የስልክ ቁጥር፦** ______________________

**ኢሜል፦** ______________________

## ተጨማሪ የወላጅ/አሳዳጊ መግለጫዎች (ግዴታ አይደለም)

**የመጀመርያ ስም፦** ______________________

**የቤተሰብ ስም፦** ______________________

**ከተማሪው ጋር ያለ ግንኙነት፦** ______________________

**የስልክ ቁጥር፦** ______________________

**ኢሜል፦** ______________________

**ተማሪው የመጀመሪያ ነዋሪ ነው ወይስ የቶሬስ ስትሬት ደሴት ነዋሪ ነው?**

☐ አይ፣ የመጀመሪያ ነዋሪም ሆነ የቶረስ ስትሬት ደሴት ነዋሪ አይደለም

☐ የመጀመሪያ ነዋሪ

☐ የቶሬስ ስትሬት ደሴት ነዋሪ

☐ የመጀመሪያ ነዋሪም እና የቶረስ ስትሬት ደሴት ነዋሪ

☐ ላለመናገር እመርጣለሁ

**ተማሪው ጥገኝነት ጠያቂ ነው ወይስ ስደተኛ ነው?**

☐ አይ፣ ጥገኝነት ጠያቂም ሆነ ስደተኛ ያልሆነ

☐ ስደተኛ

☐ የጥገኝነት ጠያቂ

☐ ላለመናገር እመርጣለሁ

**አስተርጓሚ ያስፈልጋል?** ☐ አዎ ☐ አይ

**የሚመርጡት ቋንቋ፦** ______________________

**ተማሪው የተወለደው በአዉስትራሊያ ነው?** ☐ አዎ ☐ አይ፣ የት ሃገር ነው የተወለዱት?______________________

ተማሪው Medicare ካርድ ከሌላቸው፣ እባክዎ ይህንን ክፍል ባዶ ይተዉት።

**የተማሪ Medicare ካርድ ቁጥር፦** ☐☐☐☐ ☐☐☐☐☐ ☐

**የግል ማመሳከሪያ ቁጥር፦** ☐

**የማብቅያ ቀን፦** ☐☐ / ☐☐☐☐




መመርያ ብቻ
እባክዎ የፍቃድ ቅጹን የእንግሊዝኛው ቅጂ በመሙላት ይመልሱ

Australian Government
Department of Health

## የሕጻናት የጥርስ ሕክምና ጥቅማ ጥቅሞች መርሐግብር
## የጅምላ ክፍያ መጠየቂያ የታካሚ ፈቃድ ቅጽ

እኔ፣ ታካሚው/ሕጋዊ አሳዳጊው፣ የሚከተሉት እንደተነገሩኝ አረጋግጣለሁ፡-

- በሕጻናት የጥርስ ጥቅማ ጥቅሞች መርሐግብር መሠረት ከዚህ ቀን ጀምሮ ስለሚደረገው ወይም ስለሚሰጠው ሕክምና፤
- የዚህ ሕክምና ሊሆን የሚችለው ወጪ፤ እና
- በሕፃናት የጥርስ ህክምና ጥቅማጥቅሞች መርሐግብር መሠረት ለአገልግሎቶች በጅምላ እንድከፍል እና በጥቅማጥቅሙ ካፕ ስር በቂ ገንዘብ ስለሚኖር ለእነዚህ አገልግሎቶች ከኪስ ወጭ እንደማልከፍል።

**እኔ/ታካሚው እስከ ጥቅማጥቅሙ ካፕ ድረስ የጥርስ ጥቅማጥቅሞችን ብቻ ማግኘት እንደምንችል ተረድቻለሁ።**

**ለአንዳንድ አገልግሎቶች ጥቅማጥቅሞች ገደቦች ሊኖሩት እንደሚችሉ እና የሕጻናት የጥርስ ጥቅማ ጥቅሞች መርሐግብር የተወሰኑ አገልግሎቶችን እንደሚሸፍን ተረድቻለሁ። በሕጻናት የጥርስ ህክምና ጥቅማ ጥቅሞች መርሐግብር ያልተሸፈኑ የማንኛውም አገልግሎቶችን ወጪዎች በግሌ ማሟላት እንደሚያስፈልገኝ ተረድቻለሁ።**

**የአገልግሎቶች ዋጋ ያለውን የጥቅማጥቅም ገደብ እንደሚቀንስ እና ጥቅማጥቅሞች ካለቁ በኋላ ማንኛውንም የተጨማሪ አገልግሎቶች ወጪዎች በግል ማሟላት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ።**

ማመሳከሪያ #

☐☐☐☐ ☐☐☐☐☐☐ ☐

የታካሚው Medicare ቁጥር

የታካሚ / ሕጋዊ አሳዳጊ ፊርማ

የታካሚ ሙሉ ስም

የፈራሚው ሙሉ ስም
(ታካሚ ካልሆኑ)

ቀን

ይህ ቅጽ ከተፈረመበት የቀን መቁጠሪያ አመት ጀምሮ እስከ ታህሳስ 31 ድረስ የሚሠራ ነው።

ናሙና ብቻ
እባክዎ የፍቃድ ቅጹ የእንግሊዝኛው ቅጅ በመሙላት ይመልሱ

# የአፍ ጤና መጠየቅያ

ስለ ተማሪው የበለጠ ለመረዳት እና ለእነሱ የተሻለውን እቅድ ለማዘጋጀት እንዲረዳን የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንጠይቃለን።

| | |
|---|---|
| **ተማሪው በአፍ ውስጥ ህመም አለባቸው? (ለምሳሌ በጥርስ ችግሮች ምክንያት የመተኛት ችግር)** | ☐ አዎ ☐ አይ |
| **ተማሪው በጥርስ ወይም በአፍ ችግር ምክንያት የመብላት ወይም የመጠጣት ችግር አለባቸው?** | ☐ አዎ ☐ አይ |
| **በጥርስ ወይም በአፍ ችግር ምክንያት ተማሪው በግልጽ የመናገር ችግር አለባቸው?** | ☐ አዎ ☐ አይ |
| **ተማሪው በጥርስ ወይም በአፍ ስታ ችግር ምክንያት ከትምህርት ቤት ወይም ከሌሎች እንቅስቃሴዎች ቀርተው ያውቃሉ?** | ☐ አዎ ☐ አይ |
| **ተማሪው በጥርስ ወይም በአፍ ችግር ምክንያት ፈገግ አይሉም፣ አይስቁም ወይም ጥርስ አያሳይም?** | ☐ አዎ ☐ አይ |
| **ተማሪው ከዚህ በፊት ጥርሳቸውን ታይተው ወይም ተመርምረው ያውቃሉ?** | ☐ አዎ ☐ አይ<br>አዎ ከሆነ፣ የሚታወቅ ከሆነ ቀኑን |
| **ተማሪው ባለፉት ሶስት አመታት በጥርስ መበስበስ ምክንያት ጥርሳቸውን አስሞልተው ወይም አስነቅለው ያውቃሉ?** | ☐ አዎ ☐ አይ ☐ እርግጠኛ አይደለውም |
| **ተማሪው እንደ ፍራፍሬ ጭማቂ፣ ለስላሳ መጠጦች ወይም ጨዋነት ያሉ ጣፋጭ መጠጦች ምን ያህል ጊዜ በተደጋጋሚ ይወሰዳሉ?** | ☐ በቀን ሶስት ወይም ከዝያ በላይ ጊዜ<br>☐ በቀን አንዴ ወይም ሁለት ጊዜ<br>☐ በሰምንት ጥቂት ቀናት<br>☐ በጭራሽ መባል በሚቻል ደረጃ አይወስዱም |
| **ተማሪው ጥርሳቸውን በጥርስ ሳሙና በተደጋጋሚ ለምን ያህል ጊዜ ይቦርሻሉ?** | ☐ በቀን አንዴ (ጠዋት)<br>☐ በቀን አንዴ (ማታ)<br>☐ በቀን ሁለት ጊዜ<br>☐ በቀን ከአንድ ጊዜ በታች<br>☐ በቀን ከሁለት ጊዜ በላይ |
| **ከዚህ ቀደም ልናውቃቸው የሚገቡ በጥርስ ህክምና ጉብኝቶች ወቅት ተማሪው ፍራቻ፣ ስሜት ወይም አሉታዊ ተሞክሮዎች አሉት?** | ☐ አዎ ☐ አይ |
| **በተሻለ ሁኔታ ለመቋቋም ተማሪው የሚጠቀማቸው ማንኛውም ስልቶችን ወይም ድጋፎች አሉ? ለምሳሌ, ተወዳጅ አሻንጉሊት፣ የiPhone መተግበሪያ፣ መጽሐፍ**<br>(አዎ ከሆነ፣ ዝርዝሮችን ከዚህ በታች ያቅርቡ እና እባክዎ ወደ ቀጣዩ ጉብኝት ያቅርቡት) | ☐ አዎ ☐ አይ |
| **ከተማሪው ጋር በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ የቤተሰብ አባል ወይም ሰው በጥርስ እና/ወይም በድድ ላይ ከፍተኛ ችግር አለበት?** | ☐ አዎ ☐ አይ ☐ እርግጠኛ አይደለውም |
| **የተማሪውን ጥርስ እና የአፍ ውስጥ ችግር ከመመርመራችን በፊት እንድናውቀው የሚፈልጉት ሌላ ነገር አለ?**<br>አዎ ከሆነ፣ እባክዎ ዝርዝሩን ከታች ያቅርቡ። | ☐ አዎ ☐ አይ |

መመሪያ ብቻ